# የአምባገነን መንግሥታትና የተቃዋሚ ተብዬዎች እርግማን በኢትዮጵያ
## ከበቀለ ገሠሠ

## ፩ኛ/ መግቢያ፤

ቸሩ አምላካችን ምስጋና ይግባዉና ሁሉን ነገር አሟልቶ ፈጠሮናል፤ የምድራችን ስፋት፣ የአፈሩ ለምነት፣ የወንዞችና ሃይቆች ብዛት፣ የተሟላ የተፈጥሮ ሀብት፣ ብርቱና ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበረዉ ዜጋ። ለዚህም ነበር በቀድሞ ዘመናት ኢትዮጵያ ከራሷ አልፋ ለሩቅ አገራት የምትተርፍ የዳቦ ቅርጫት ተብላ የተሰየመችዉ። ዛሬ ግን ያለችበትን እጅግ አሰቃቂ ሁናቴ ስንመለከት 'የዐባይን ልጅ ዉሃ ጠማዉ' ማለት ሲያንሰን ነዉ። በተለይ ሰሞኑን በሳዑዲ አረቢያ ብቻ ከመቶ ሺህ በላይ ወገኖቻችን ተቀጠቀጡ፣ ተሰቃዩ፣ ተደፈሩ፣ ተራቡ፣ ተጠሙ፣ ተወረወሩ፣ ተገደሉ። ከሁሉም የሚያሳዝን ደግሞ ይሄ ሁሉ ሰቆቃ ሲደርስ መንግሥታችን እጎናቸዉ አለመቆሙ አንሶ ብሶት ለማሰማት ሰላማዊ ሰልፍ የወጡትን (እናቶች ጭምር) ሲገርፍና ሲያስር መገኘቱ ነዉ።

የሕዝባችን መከራና ሰቆቃ እየከፋ ሄደ። ለዚህም ሰቆቃ የተፈራረቁት አምባገነን መንግሥታትና ተቃዋሚ ተብዬዎች ሁለቱም ሊጠየቁበት ይገባል ብዬ አምናለሁ። የተጨቆነዉ ሕዝብ ተነሳስቶ ለመብቱ ሲታገል ጨቋኝ መንግሥታት ለዉጥ እንዲያደርጉ ይገደዳሉ፣ ካለዚያ በተባበረዉ የሕዝብ ኃይል ተንኮታኩተዉ ይወድቃሉ። የታገለዉ ለዉጥ ያመጣል፤ ያልታገለዉ ቁጭ ብሎ በባርነት ሲገዛ ይኖራል፣ ቁጭም ባለበት ይሞታል ማለት ነው። የለዉጥ ባለቤት ሁሌ ሕዝብ መሆን አለበት። ህዝቡ ትግሉን በሚገባ እንዲያቀናጅ የትግል መሪ ይፈልጋል። ስለዚህ የተቃዋሚ የፖሊቲካ መሪዎች ታላቅ ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል። ያገራችንን ጭብጥ ሁኔታ ስንመረምር ግን በሁለቱም በኩል ታላላቅና ተደጋጋሚ ድክመቶች ታይተዋል። አምባገነን መንግሥታት ለዘለዓለም ካልገዛን ሲሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች ኅብረታቸዉን ማጠናከር ስላልቻሉ የጨቋኝ መንግሥታትን ዘመናት ሲያራዝሙ ቆይተዋል። ባለፉት ሁለቱና ባሁኑም መንግሥታት የታዩትን ችግሮች በራሴ እይታ እንደሚከተለዉ ባጭሩ ለመመርመር እሞክራለሁ፤ አሁንም ካለፉት ሃፍረቶችና ቅሌቶች እንድንማር ደጋግሜ ለመጎትጎት ብዬ እንጂ ያለፈዉን መራራ ቁስል ለማስታወስ ፈልጌ እንዳልሆነ በጥሞና ላሳስብ እወዳለሁ።

## ፪ኛ/ በግርማዊ ጃንሆይ ዘመነ መንግሥት

### ሀ) የሥርዓቱ አመጣጥ፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

ከታላቁ ዐፄ ምንሊክ ቀጥሎ ሥልጣን ላይ መዉጣት የነበረበት ልጅ እያሱ ወይስ ተፈሪ? የሚለው ጥያቄ ብዙ ሲያወዛግብ የኖረ ሃቅ ነዉ። ያም ሆነ ይህ፣ የወቅቱ የኃይል ሚዛን ወደ ተፈሪ ስላመዘነ ልጅ እያሱ ተወግዶ፣ ንግሥት ዘዉዲቱ ሽግግሩን ይዘዉ በመጨረሻ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለዙፋን በቁ። በሥልጣን ዘመናቸዉም ዘመናዊ ሕገ መንግሥት ወጣ፣ ለወጉ ፓርላማ ተከፈተ፣ ብዙ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች፣ ክልኒኮች፣ ሆስፒታሎች፣ ወዘተ ተገነቡ። ካገርም ዉጪ አፍሪቃ አገሮች ከቅኝ ግዛት ነፃ እንዲወጡ ታላቅ ዕርዳታ ተለገሰ። ሰሜንና ደቡብ ሱዳኖች እንዲስማሙ ታላቅ አስተዋጽዖ አደረጉ። ለአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ምሥረታ ቁልፍ ሚና ተጫወቱ። ከዐለም መንግሥታት ምሥረታ በፊት በነበረዉ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ዉስጥም አገራችንን አባል በማድረግ ብዙ ጥረት አድርገዋል።

ሆኖም ግን አገዛዙ የባላባታዊ ሥርዓት ስለነበረ በተለይ ጪሰኞች ክፉኛ ተጨቆኑ። ድህነትና ርሃብም ተደጋገሙ። የመሬት ይዞታንና የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን መመለስ አቃታቸዉ። ያገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚፈለገዉን ያህል ሊንቀሳቀስ አልቻለም።

### ለ)	የተቃዋሚዎች ሚናና ችግሮች

ሥርዓቱን ለመጣልና ዲሞክራሲን ለመገንባት በተለይ ከ1950ዎቹ ጀምሮ ግልጽ ትግል ተጀመረ። ባንድ ወቅት ግርማዊ ጃንሆይ ከአሥመራ ሲመለሱ ደሴ ላይ ሊቀበላቸዉ የሄደዉ የራሳቸዉ ጠባቂ የክብር ዘበኞች አዛዥ ጄነራል መንግሥቱ ነዋይ አንድ አሰቃቂ ነገር ይመለከታል። የተጨቆኑት የወሎ ጪሰኞች ባንገታቸዉ ላይ ቀንበር አስረዉ ፊታቸዉ ቀርበዉ አቤቶታ ያቀርባሉ። ጄነራል መንግሥቱ ከአዲስ አበባ ወጥቶ ስለማያቅ ችግሩ ያን ያህል መሆኑን ኤአቅም ነበረ። በፊት ታናሽ ወንድሙ ገርማሜና ቆራጥ የትግል አጋሩ ወርቅነህ ገበየሁ ሲወተዉቱት ያልሰማዉ ጄነራል ከዚያን ቀን ጀምሮ ከፍተኛ ሥልጣኑንና ጥቅሙን መስዋዕት በማድረግ በንጉሡ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ ሙከራ አደረገ። ዳሩ ግን በዘመኑ በቂ ተመክሮ ባለመኖሩና ባንዳንድ የዉስጥም የዉጪ ራስ ወዳዶች ሻጥር ሊከሽፍ ቢበቃም ታላቅ ምሣሌ ጥሎ አለፈ። ወዲያዉኑ በዓለም እጅግ በጣም ዝነኛ የነበረዉ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ተጀመረ። በተቀናጀ የሕዝብ  ትግል የታላቁ ንጉሠ ነገሥት የአገዛዝ ዘመን አከተመ።

## ፪ኛ/ የወታደራዊ አገዛዝ ዘመነ መንግሥት

### ሀ)	የሥርዓቱ አመጣጥ፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

የንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን ሲወድቅ በወቅቱ የተደራጀ የተቃዋሚ የፖሊቲካ ፓርቲ ባለመኖሩ የሕዝቡ ትግልና ድል በመለዮ ለባሾች ተቀማ። ነገር ግን ምንም እንኳን የፖሊቲካ አስተዳደር ብቃት ሳይኖረዉ በእጁ ባለዉ ጠብ መንጃ ተመክቶ ሥልጣን ላይ ቢቆናጠጥም ብዙ መልካም ለዉጦች አሳይቷል፣ የመሬት አዋጅ ሙከራ፣ መሠረተ ትምህርት፣ የመንገዶች፣ ድልድዮች፣ ክሊኒኮች፣ ሁስፒታሎች፣ ኮሌጆች፣ ወዘተ ግንባታዎች። ነገር ግን ዲሞክራሲ ታፈነ። ሕዝብ ለሚያሰማዉ የዲሞክራሲ ጥያቄዎች ምላሽ ርሸና ሆነ። በዓለም ታይተዉ የማይታወቁ ፋሺስታዊ እርምጃዎች ተወሰዱ፣ ማሰር፣ መደብደብ፣ ማሰቃየት፣ መረሸን፣ ወዘተ። የንጹሐን ወጣቶች ሬሳ መንገድ ላይ አሳደሩ፣ እናቶች የልጆቻቸዉን አስከሬን ተቀብለዉ ለመቅበር 'የባከነዉ' ጥይት ዋጋ እስከማስከፈል ደረሱ፣ እቀብር ላይ ልቅሶ እንኳን ተከለከለ። አብዮት ልጇን ትበላለች፣ የፊዴል ወጠጠ እየተባለ ተዘፈነብን።

### ለ)	የተቃዋሚዎች ሚናና ችግሮች

ከዝነኞቹ የተማሪዎች፣ መምህራን፣ ሠራተኞች፣ ወዘተ እንቅስቃሴዎች የፈለቀዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ቅልጥ ያለ ትግሉን አቀጣጠለ። እንደነመኢሶን  የመሳሰሉት ድርጅቶች ግን ከደርግ መንግሥት ጋር ወገኑ። ምናልባት የኢሕአፓ አባላት ተጠራርገዉ ካለቁ በኋላ ሥልጣኑን 'ከሞኝና መሃይም' ወታደሮች እጅ በቀላሉ ለመንጠቅ የሚችሉ መስሏቸዉ ይሆን ይሆናል። በኋላ ግን ደርግም ነቃባቸዉና እነርሱንም ጠራርጉ ከኢሕአፓና ከሌሎች ጠላቶቹ ጋር ባንድ ጉድጓድ ቀበራቸዉ። 'በቁማቸዉ ጎን ለጎን ቁመዉ በህብረት መታገል ያልቻሉት የኢትዮጵያ ልጆች ባንድ ጉድጓድ ተከተቱ' ተብሎ በታሪክ ተመዘገበ።  ኢሕአፓም በርግጥ አንዳንድ ስህተቶች ፈጽሟል፣ የኢትዮጵያና ሃቀኞች ልጆቿ ጠላቶች ብዙ ናቸዉ፣ በጎረቤት፣ በመካከለኛዉ ምሥራቅ አገሮች፣ በምዕራቡ ኃይሎች ድጋፍ እስከ አፍንጫቸዉ ድረስ የታጠቁ ሻእቢያና ወያኔ ባንድ በኩል፣ በሌላዉ ደግሞ በሶቪዬት ህብረት እንደዚሁ እስከ አፍንጫዉ ድረስ የታጠቀዉ የደርግ ሠራዊት እንደነበረ ይታወሳል። ሌላዉ የሻእቢያና የወያኔ ጥምር ሤራ ደግሞ ኢሕአፓን

መስለዉ ቀርበዉ ራስ ቢትወደድ አዳነን መግደላቸዉ ነበር። ራስ ቢትወደድ አዳነ እጅግ በጣም የተከበሩ ጀግና፣ አገር ወዳድና ደግ ሰዉ እንደነበሩ ታሪክ ሲያስታዉሳቸዉ ይኖራል። የወልቃይት ጠገዴ ጀግኖች በስህተት ተነሳስተዉ በኢሕአፓ ላይ ትልቅ ጉዳት አደረሱ። በነዚያ የዉስጥና የዉጪ ጥምር ጠላቶች የተከበበዉ ኢሕአፓ እጅግ በጣም አሰቃቂ አረመኔያዊ ቀይ ሽብር ሲታወጅበት ዐቅሙን ዐዉቆ ታክቲኩን ቀይሮ ወደባላገር ማፈግፈግ ሲገባዉ አዲስ አበባ ላይ ፊት ለፊት በመጋፈጡ ምክንያት ብዙ ጉዳት ደረሰበት። ይሄን ስህተት ፓርቲዉ ራሱ አምኖ በመቀበሉ ግን ክብር ይገባዋል።

ለማናቸዉም፣ ከዚያ በኋላ ደርግ ልቡ አበጠበት፣ በሥልጣን ሰከረ። የገዛ ጄነራሎቹን እንኳን ምክር አልቀበል አለ፣ ጭራሹንም እንደጠላቶች ቆጥሯቸዉ በላቸዉ። ከዚያ በኋላ አዉራ ያጣዉ ጀግናዉ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሃሞት ፈሰሰ፣ ተስፋ ቆርጦ አፈገፈገ። ‘ቆራጡ አብዮታዊ መሪ’ ፈርጥጠዉ ሃራሬ ገቡ። የመንግሥት ሥልጣን ክፍተት ተፈጠረ።

## ፬ኛ/ የወያኔ/ኢህአደግ አገዛዝ

### ሀ) የሥርዓቱ አመጣጥ፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሤ ለኤርትራ የተሰጠዉን ፌደራላዊ ግንኙነት ሲያፈርሱ የጀብሀ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ጀብሀ ሲዳከም ሸአቢያ ተተክቶ በኤርትራ የብዙ ዓመታት ትግል መራ። ወያኔንም እያጠናከረ መራራ ጦርነቶች ሲያካሂድ ኖረ። ሆኖም ግን የመገንጠል ጥያቄ ሊዋጥላቸዉ ያልቻለዉ የኢትዮጵያ ሠራዊት ያገሩን አንድነት ለመጠበቅ ደህና አድርጎ ሲመክትና ሲዋደቅ ኖረ። በመጨረሻዉ ግን እላይ እንደተጠቀሰዉ ደርግ በገዛ ኃጢአቱና በሕዝባችን የረጅም ጊዜ ቆራጥ ትግል ኃይሉ መነመነ። እንግሊዞችና አሜሪካኖች ኮ/ር መንግሥቱ ወደሃራሬ እንዲኮበልሉ ካመቻቹ በኋላ በለንደን ላይ በሂርማን ኮህን ሰብሳቢነት የዉሸት ‘የሰላም ኮንፌረንስ ተጠራ። በኮንፌረንሱ ላይ ህብረ ብሔራዊ የሆኑት ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዲሳተፉ አልተፈቀደም። ለሦስት ቀናት የታሰበዉ ጉባኤ በግማሽ ቀን ተጠናቀቀ። ቀድመዉ የወሰኑትን ዉሳኔ በግልጽ አበሰሩ። የተፍረከረከዉ የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑካን ወደ አሜሪካ አቀና። በዚህ ምክንያት ለአያሌ ዓመታት በጦርነት ማሸነፍ ያልቻሉት ሻእቢያና ወያኔ በለስ ቀናቸዉ። ካለምንም እንቅፋት ሰተት ብለዉ ባቋራጭ በምዕራቦቹ ቡራኬ ጭምር ለሥልጣን በቁ።

እነዚህ ኃይሎች በትግል ላይ በነበሩበት ጊዜ ያራምዱቸዉ የነበረዉ በተለይ የመገንጠል ጥያቄ ብዙ ኢትዮጵያዉያንን  ሲያሳዝን የኖረ ቢሆንም ቅሉ ዕድል አግኝተዉ ወደሥልጣን ሲመጡ ከደርግ የባሰ መንግሥት አይመጣም በማለት በቀና ፊት ተቀብሏቸዉ ነበር።

ሥልጣን ላይ ከወጡ ጀምረዉ ብዙ ግንባታዎች ዘርግተዋል፣ ፌደራላዊ መንግሥት ለማቋቋም መሞከር፣ ሰማይ ጠቀስ ፎቆችና ወለላ መንገዶች መሥራት፣ ወዘተ። በጎኑ ግን ከፈጸሟቸዉ ከባድ ጥፋቶች መሃከል እታች ባጭሩ የተመለከቱትን ማየት ይቻላል፣

- የኢትዮጵያን መከላከያ ጦር፣ የፖሊስ ሠራዊትና ሲቪል ሠራተኞች በመበተን ስንት መቶ ሽህዎች ድሆች ዜጎች ለከባድ ሲቃይ ተዳርገዋል፣ ቋሚ የሲቪልና የመከላከያ ሠራዊት  አገልግሎት ሳይኖር ተቀጥያ ያለዉ የአገር ህልዉና መጠበቅ ሆነ ዕድገት ሊመጣ እንደማይችል ሊገነዘቡ አልቻሉም።
- በኢትዮጵያና  በኤርትራ ህዝብ መሃል ለብዙ ሺህ ዓመታት የነበረዉን ትስስር ቆርጠዋል፣

- የሪፈረንደሙ አካሄድ በፍጹም ትክክል አልነበረም፤ 'ነጻነት ወይስ ባርነት?' ብቻ ከማለት ለምን ሌሎቹም አማራጮች አልተካተቱም?
- አጣድፈዉ ካስገነጠሉ በኋላ የባድሜን ጦርነት ምክንያት በማድረግ መሀል አገር በሰላም ለዘመናት የኖሩትን የኤርትራ ዜጎች ለቃቅሞ ማባረርና ቤተሰቦች ማሰቃየት ተገቢ አልነበረም፤
- ጎሣን ከጎሣ፤ ሃይማኖትን ከሃይማኖት ጋር ማጋጨት፤
- አማራዉን ነጥሉ የማርያም ጠላት ማስመሰልና ማሰቃየት ትልቅ ኃጢአት ነዉ፤ ባለፉት በተፈራረቁ ጨቋኝ ሥርዓቶች ሥር በጎጃም፤ በጎንደር፤ በደብረ ብርሃን ወዘተ የሚኖሩት ጭቁን ዜጎች ከሌላዉ ወገን የተሻለ ምንም ጥቅም እንዳላገኙ የተሰወረ ሃቅ አይደለም። ለአገር አንድነትና ነጻነት መቆርቆር ደግሞ እንደጠላት የሚያስቆጥር መሆን አልነበረበትም።
- ከሽአቢያ ጋር በመተባበር ደብዛቸዉን ያጠፏቸዉን የኢሕአፓ ሃቀኞችና ቆራጥ መሪዎች የነበሩትን እንደነ ጸጋዬ ገ/መድህን (ደብተራዉ)፤ ስጦታዉ ሁሴን፤ አረጋሽ በርታና በለጠ ዓምሓን ዬት እንደጣሏቸዉ እስካሁን ድረስ የተናገሩት ነገር የለም፤ ለመሬት ላራሹ፤ ለዲሞክራሲና ለወገን ብልፅግና ቆርጠዉ ከመታገል በስተቀር የፈጸሙት ምንም ኃጢአት ባለመኖሩ በታሪክ ፊት ያስጠይቃቸዋል።
- ዲሞክራሲ ታፈነ፤ የፖሊቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶችና የነጻ ዜና አገልጋዮች እንደጠላት ተፈረጁ፤ ታሰሩ፤ ተሰቃዩ፤ ተሰደዱ፤
- የተማረዉ ክፍል ተገለለ፤ አገሪቷ እጅግ ለፍታ ያስተማረቻቸዉ ልጆችዋ ካላገለገሏት ማን ሊያሳድጋት ነዉ? ባለፉት 30-60 ዓመታት ደህና የተማሩና የሥራ ልምድ ያካበቱትን ባለሙያዎች የሲቪል ኮሌጅ ለብለብ ምሩቃን ሊተኳቸዉ አይችሉም። በነዚያ አያሌ ዘመናት አገሪቷ ለፍታ ያስተማረቻቸዉን ዜጎች እንዲተኩ ከኢስያና ከምዕራብ አፍሪቃ የሚቀጥሯቸዉ አስተማሪዎች አገሪቷን ስለማያዉቋት ምንም እርባታ ማምጣት እንደማይችሉ ሳያዉቁት ቀርተዉ አይደለም። 'ያገሩን ሠርዶ ባገሩ በሬ' የሚለዉነ መርህ ጥሰዉ አገሩን በሬ አመከኑ። ባገሩ መኖርና መሥራት ያልቻለዉ ንፁሕ ዜጋ ተበትኖ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችንና መዕራባዉያን አገሮችን ሲያገለግሉና ሲያቀኑ ይገኛሉ፤ ምንኛ ያልታደለና የባከነ ትዉልድ!!1
- የአገሪቷ ንብረት በሙሉ በራሳቸዉና በደጋፊዎቻቸዉ እጅ ብቻ ከወደቀ ብዙሃኑ ዜጋ ምን ሊበላ ነዉ?
- ሕዝብን እያፈናቀሉ ሚሊዮን ሄክታሮች ለዉጪ ዜጎች መስጠት ዘለቄታ ያለዉ ምን ዓይነት አገራዊ ዕድገት ሊያመጣ ይችላል?
- በርሃብና በችጋር የተጠበሰዉን ዜጋ ከባርነት በማይሻል ሁኔታ ለዐረብ አገሮች ማመቻቸት ኃጢአት አይደለም ወይ?
- ይባስ ብሎ በዐረብ አገሮች ሲቀጠቀጡ፤ ሲደፈሩ፤ ሲሰቃዩና ሲገደሉ እጎናቸዉ አለመቆምና አለመከላከል ከሁሉም የበለጠ ኃጢአት መሆኑ እንዴት ተሳናቸዉ?
- ብዙ ብዙ ተመሳሳይ አላስፈላጊ ችግሮች።

## ለ) የተቃዋሚዎች ሚናና ችግሮች

እላይ እንደተገለጠዉ ከመግባታቸዉ በፊት በለንደን ላይ በተዘጋጀዉ የይስሙላ 'የሰላም' ጉባዔ ላይ የተሳተፉት መገንጠልን የሚያራምዱ የፖሊቲካ ኃይሎች ብቻ ነበሩ። እነ ኦነግ ተከትለዉ ገብተዉ የሽግግሩን ቻርተር ፈርመዉ ተቀላቀሉ፤ ብዙም ሳይቆዩ በሥልጣን ድልድል ተጋጭተዉ በገቡበት አይሮፕላን ካገር ኮበለሉ። አንዳንዶቹ በግልም በቡድን እየሆኑ ካሜሪካና ካዎሮፓ ዘልለዉ ሄደዉ አንዳንድ ቦታዎች ይዘዉ ጠገኗቸዉ።

ብዙዎቹ እንደዚሁ እየተጋጩ አንዳንዶቹ ለእስራት በቁ፤ ወደስደትም 'ተቃዉሞ ትግልም' ተመለሱ።

እዚህ ላይ በ2003 ዓ/ም ስለተፈጠረዉ ህብረት ትንሽ ልጠቅስ እወዳለሁ። የሕዝቡ ብሶት እየተባባሰ በመምጣቱ ምክንያት ባገርም ሆነ በዉጪ ያሉት ወገኖች ተነቃንቀዉ አስፈሪ ትግል ጀመሩ። በ2003 ዓ/ም (በፈረንጆች አቆጣጠር) 15 የተቃዋሚ ፖሊቲካ ድርጅቶች ለ15 ቀናት በር ዘግተዉ ተወያይተዉ ተማምለዉ ህብረት ፈጠሩ። እነ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዮስና፤ ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን የመሳሰሉ እጅግ በጣም የተከበሩ አባቶች ተሳትፈዉ ግሳጼ፤ ምክርና ቡራኬ ሰጧቸዉ። ይሄም ለሰላም ወዳድ ወገኖች በሙሉ ታላቅ ብሥራት ነበረ። የህብረቱም ሠነድ የሚከተሉትን ታላላቅ ስምምነቶች ያካተተ ነበር፤

- ትግሉ በሰላማዊ መንገድ እንዲሁን፤
- በታቀደዉ የ2005 ዓ/ም አገራዊ ምርጫ ላይ ለመሳተፍ የሚከተሉት አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸዉን ማረጋገጥ፤ ነፃ የምርጫ ቦርድ መመስረትና በያንዳንዱ ምርጫ ኬላ ላይ ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ገለልተኞች ታዛቢዎች መገኘት እንደሚኖርባቸዉ፤
- ሁሉም የፖሊቲካ ድርጅቶች እኩል እንዲሳተፉ ሁኔታዎች መመቻቸት እንደሚኖርባቸዉ፤
- እነዚህ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ግን ከምርጫዉ መገለልና የሕዝብ ሰላማዊ አመፅ መምራት ግዳጅ መሆን እንዳለበት ተስማምተዉ ተፈራረሙ።

ዳሩ ግን ተደጋጋሚ ዕድላችን ሆነና ገና ዓመት ሳይሞላቸዉ አንዳንድ አባላት ህብረቱን ጥለዉ ወጡ። በህብረቱ ጎን ቅንጅትን ፈጠሩ። አሁንም ተስፋ ሳይቆረጥ ህብረትና ቅንጅት የጋራ ትግል ለማካሄድ ተስማሙ። እጅግ የሚያሳዝነዉ ግን በነዚህ ስምምነቶችና ቃልኪዳኖች ብዙም መግፋት አልተቻለም።

ይባስ ብሎም ብዙ አባላት የነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሥነ ሥርዓት ቅድመ ሁኔታዎች ገና ሳይሟሉ የሕዝባችንን ጥያቄ ንቀዉ ዘልለዉ በምርጫዉ ዉስጥ ተሳተፉ። ከዚያ በኋላ የደረሰዉን አሳዛኝ ድርጊትና የሕዝባችንን ተደጋጋሚ ሰቆቃ ሁሉም ዜጋ የሚያዉቀዉ ነዉ። ዛሬ ሕዝባችን እጅግ በጣም በመሰቃየት ላይ እንዳለ የማያዉቅ ንፁሕ ዜጋ ኤኢኖርም፤ ኩሩ የነበረች ዉድ አገራችን ተንቃለች፤ ተደፍራለች፤ ከዚህ በላይ ምን እንደሚጠበቅ ከቶ ሊገባኝ አልቻለም።

## ፩ኛ/ አሁንም ካለፉት ስህተቶችና ጥፋቶች መማር አንችልም ወይ?

ወያኔ/ኢሕአደግ ለዘለዓለም ሊገዛ አይችልም፤ ለሁሉም ጊዜ አለዉና። በዓለም ታላቅ ዝና ያተረፉት የግ/ቀ/ኃ/ሥና በአፍሪቃ አህጉር መሬትን ያንቀጠቀጠዉ የደርግ መንግሥት ቀናቸዉ ሲደርስ እንዴት እንደመነመኑና እንደከሰሙ መዘርዘር አይኖርብኝም፤ በታሪክ ፊት ተቀምጧልና። በሩቁም በእነ አሜሪካ ለረዥም ዓመታት ሲረዱና ሲደገፉ በነበሩት በእነ ሞቡቱ፤ የሻህ ንጉሥ፤ ሆስኒ ሙባረክ፤ ወዘተ ላይ በመጨረሻ የደረሰዉን ዉርደት መገንዘብ ያስፈልጋል።

ተቃዋሚ የፖሊቲካ ድርጅቶች ነን የሚሉትና በተግባር ግን የጭቆናን ዘመን የሚያራዝሙ በሙሉ ካለፉት ስህተቶች ገና ሊማሩ አልቻሉም፤ 'ድር ቢያብር አንበሳ ያስር' የተባለዉን ቅዱስ አሳብ ደጋግመዉ መናቃቸዉ ያስተዛዝባል። ቁርጥ ያለ አቋም ያስፈልጋል፤ ከዛፍ ዛፍ መዝለል ፄትም አያደርስም። ለጊዜያዊ ጥቅማ ጥቅሞች በርካሽ መገዛትና አገርን መሸጥ በሰማይም

*በምድርም ያስጠይቃል። ቀኑ ሲደርስ ራቆታችንን ወደምድር እነደመጣን ሁሉ ራቆታችንን ወደዚያዉ እነደምንመለስ አንርሳ!!!*

*ምርጫዉ በጣም ቀላል ነዉ፤*

- *ህብረት ማጠንከር የግድ ነዉ፤ ካለዚያ አገራችንን ለማዳከም ወይ ለማጥፋት ለሚፈልጉት ጠላቶች መጋለቢያ ቦታ ሆነን እንቀራለን። በዚያ ደግሞ የሚደሰት ማንም ዜጋ ይኖራል ብዬ መገመት አልችልም። ወደ 2003 ዓ/ም ስምምነት ብንመለስ ይሻላል። ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች ተቀራርበዉ በዲሞክራሲ ግንባታ ላይ መተባበር ይኖርባቸዋል። እንዲያዉ ቂጭ ብለን ወያኔ/ኢሕአደግ፤ አሜሪካና ሌሎች የዉጪ መንግሥታት የሚቀጥለዉን መንግሥት ያመቻቹልናል ብሎ መጠበቅ 'ዉሃ ቅዳ ዉሃ መልስ' ብቻ ነዉ የሚሆነዉ። ካሁንም ወዲያ ቁጭ ብሉ በተደጋጋሚ የሚታለል ዜጋ አይኖርም።*
- *የፃ ዜና አገልግሎት ድርጅቶች/ሚዲያ ነን የሚሉት ሁሉ በቅንነት ሁሉንም ዜጎችና ድርጅቶች ማሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። ከተሰቃዩ፤ ከታሰሩ፤ ከተሰወሩና ከተገደሉ ንፁሓን ዜጎች መካከል እየመረጡ ማቅረብና ሌሎቹን መርሳቱ የሙያ ጉድለት ስለሚሆንና ስለሚያስተዛዝብ የተሻለ ጥረት እንዲደረግ ጨምሬ ላሳስብ እወዳለሁ።*
- *አገራዊ እርቀ ሰላም ማዉረድ የተባረከና ቀና ተግባር ነዉ። ከኒልሰን 'ማዲባ' ማንዴላ ጥረቶች ትንሽ ብንማር መልካም ነዉ። እርሳቸዉ ለአገራቸዉ ነፃነትና ሰላም ሲሉ ከአፓርታይድ ጠላቶቻቸዉ ጋር እንኳን ታርቀዋል። አሁን ያለፈዉ አለፈ። ይቅር መባባል አለብን። ለወደፊቱ መልካም ራዕይ ፈጥረን አገራችንን ከጥፋት ማዳን አለብን። በሕዝብ ተመርጠዉ በሕዝብ መሃል በነፃ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉና ሕዝባችንን ተንከባክበዉ አገራችንን ወደ ጥፋት ሳይሆን ወደ ዕድገት ጎዳና ሊመሩ የሚችሉትን መሪዎች መፍጠር አለብን። በተለይ ከኤርትራ ወገኖቻችን ጋር ሰላም መፍጠር አለብን፤ ተወደደም ተጠላ የብዙ ሺህ ዓመታት የጠበቀ ትሥሥር አለንና። የፈለገዉን ዓይነት መንግሥት የመመሥረት ኃላፊነት የኤርትራ ሕዝብ ነፃ ምርጫ ነዉ። ያ እንዳለ ሆኖ ግን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋራ የጠበቀ የኢኮኖሚና ማህበረሰባዊ ግንኙነትና ትብብር መፍጠር ለሁላችንም ይበጃል የሚል ግምት አለኝ። ዛሬ ባገራችን በእንቬስትመንት መልክ እየገቡ የሚጠቀሙት የሩቅ ዘጎች ናቸዉ። የዚያ እንቬስትመንት ቅድሚያ ለኤርትራ ወገኖቼ ቢሰጥ ምኞቴ ነዉ። በኤርትራም በኩል የምጠይቀዉ ጥያቄ አለኝ፤ እነርሱ በጎናቸዉ ምጽዋን የሚያክል ወደብ ይዘዉ ሳለ እኛ የባሕር በር ተዘግቶብን ስንሰቀይ ምንም ጠቀሜታ ሊሰጣቸዉ የማይችለዉን የሩቁን አሰብ ዘግተዉ መቀመጣቸዉ የረባ ትርጉም አይኖረዉም። ስለዚህ መቀራረብ፤ መደጋገፍና ሕዝቦቻችን መታደግ የተቀደሰ ዓላማ ነዉ ብዬ ከልቤ አምናለሁ።*
- *ለዚህም መፍትሔዉ ንጹሕ ዲሞክራሲን መገንባት ብቻ ነዉ።*
- *በዓለም እንደአሸዋ የተበተነዉ ወገን ተመልሶ በኩራት እየኖረ ሕዝባችንን እንዲያገለግል ጥርጊያ መንገድ ማበጀት ይኖርብናል።*
- *እግዚአብሔር የሰጠንን ሰፊ የተፈጥሮ ኃብት ለወገኖቻችን ማብቃትና ርሃብን፤ ጥማትን፤ እርዛትን፤ ስደትንና እንግልትን ለማስወገድ ቆርጦ መነሳት ያስፈልጋል።*

## *ፈሩ አምላካችን ቅን ልቦና ይስጠን፤ ይታረቀን፤ ወገኖቻችንና ውድ አገራችንን ይጠብቅልን፤ አሜን*